# የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በትግራይ ክልል በአካል በመገኘት ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ምርመራ እንዲያካሂድ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግለት

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የዜጎች ሰብዓዊ መብት በምንም ምክንያት እና በማንኛውም ጊዜ ለድርድር የማይቀርብ እንደሆነ ያምናል። ሕወሃት በኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊታችን ላይ የፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ ከተወሰደው የሕግ የበላይነትን እና የሀገር አንድነትን የማስጠበቅ እርምጃ በኋላ የኢዜማ ከፍተኛ አመራሮች የሚመሯቸው ቡድኖች ወደቦታው አቅንተው ነዋሪዎችን ማነጋገራቸው ይታወሳል። ይህን ጉዞ ተከትሎ በሰጠነው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በሁሉም አካባቢዎች አስቸኳይ የሰብዓዊ እርዳታ እንደሚያስፈልግ እና ይህንኑ በማሰባሰብ እና በማድረስ ሂደት ውስጥ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በነቂስ እንዲሳተፉ ጥሪ አስተላልፈን ነበር። በክልሉ የተቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር እና የፌደራል መንግሥት ሰብዓዊ እርዳታው በፍጥነት እንዲደርስ ከማድረግ እና ከማመቻቸት ባለፈ በሁሉም አካባቢዎች መደበኛ የሰላም እና ሕግ ማስከበር ሥራ የሚሠሩ መዋቅሩች እንዲዘረጉ እና ሥራቸውን በፍጥነት እንዲጀምሩ የሚያስችል ድጋፍ እንዲያደርጉ አሳስበን ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ሕወሃት በኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ላይ ያደረሰውን ጥቃት ተከትሎ የሌላ ሀገር ወታደሮች የሀገራችንን ድንበር አልፈው ገብተው ከነበረ እና መቼ የሀገራችንን ድንበር ለቀው እንደሚወጡ መንግሥት ለሕዝብ ግልፅ እንዲያደርግ መጠየቃችን ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እያለ አምነስቲ ኢንተርናሽናል «የአክሱም ጭፍጨፋ» በሚል ርዕስ ባወጣው ዘገባ በትግራይ ክልል አክሱም ከተማ በኅዳር ወር በተለይ በኤርትራ ወታደሮች የጅምላ ግድያ፣ ለሰላማዊ ዜጎች ደህንነት ጥንቃቄ ያላደረገ የከባድ መሣሪያ ድብደባ እና ዘረፋ ሆን ተብሎ ተፈጽሟል ብሏል። አምነስቲ በዚህ ዘገባው በአክሱም ከተማ ተፈጸሙ ያላቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የጦር ወንጀል ተብለው ሊመደቡ የሚችሉ እንደሆኑ ጠቅሷል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) መንግሥት የሀገር ሰላም እና አንድነትን ለማስጠበቅ ተገዶ የገባበትን እርምጃ በወሰደባቸው ቦታዎች ዜጎች ላይ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አስፈላጊው መጣራት ተደርጎባቸው ተጠያቂነትን ማስፈን የሚያስችል እርምጃ መወሰድ አለበት ብሎ ያምናል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈፅሞባቸዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ቦታዎችን ድረስ በአካል በመሄድ አስፈላጊውን ምርመራ እንዲያደርግ እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ይህንን ምርመራ ለማድረግ የሚያስፈልገውን እገዛ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር እና የፌደራል መንግሥት እንዲያደርጉ በአፅንዖት እንጠይቃለን። ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማትም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በቦታው ድረስ በአካል በመገኘት የሚያደርገውን ምርመራ በተሻለ ብቃት ለማድረግ የሚያስፈልገው ድጋፍ ካለ ኮሚሽኑ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት እገዛ እንድታደርጉ እንጠይቃለን።

የኢዜማ ሕዝብ ግንኙነት

የካቲት 20 ቀን 2013 ዓ.ም